# ኮብል ስቶንን ማን ይቅበራት? ስደተኛው? ጨለምተኛው? ትምክህተኛው?

ሠይፈ ደርቤ

‹‹የተማረ ይቅበረኝ አለች ኮብል ስቶን›› ከሚለው የፌስ ቡክ ተረት ጀምሮ ‹‹ድንጋይ ለመጥረብ ከሆነ መማር ለምን ያስፈልጋል? የዩኒቨርስቲ ምሩቃንም ሆኑ ወላጆች ተስፋ ቆርጠዋል፤›› የሚሉ ወሬዎች ኃላፊነት ከማይሰማቸው ወገኖችም፣ በስራ ባህል ጉዳይ ከፍተኛ የአመለካከት ችግር ካለባቸው ተስፋ የቆረጡ ባለሙያዎችም፣ እንደ አቅሚቲ ፖለቲከኞች ነንና ይህቺን አጀንዳ የወጣቱን ቀልብ እንግዛባት ያሉ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችም ያራግቧት ጀምረዋል፡፡

ስንት የህክምና ዶክተሮች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ ኢንጂነሮች ወዘተ... የተሻለ ገንዘብ ቋጥሮ ለመምጣት በሚል የተማሩባትን ሀገር ኢትዮጵያ ጥለው በአሜሪካና አውሮፓ ከተሞች ሽንት ቤት ሲያጥቡ፣ በጥበቃ ስራ ሲሰማሩ፣ የምግብ ሰሃን ሲወለውሉ ስለ ስራው መጥፎነት ተናግሮ የማያውቅ አንደበት ‹አገሬ እንዳቅሟ ስራ ፈጠረች፣ የፈጠረችውን ስራ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሊሰሩት ነው› ብሎ መብገንን ምን አመጣው፣ ይህን ፌዝ ምን አመጣው ይሆን?

ከዛሬ 3 እና 4 ዓመት በፊት በሀገራችን የገበያ ስርዓት በማስያዝና ምርቶቻችን ዓለም አቀፍ እውቅናና ጥራት እንዲኖራቸው በማድረግ ከፍተኛ ባለውለታ በሆነው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተቀጥረው ከሚሰሩ ከፍተኛ የማኔጅመንት ሰዎች በአንዱ የተነገረውን በደምሳሳው እናስታውስ፡፡

‹‹ በውጭ ሀገር ነው የተማርኩት፤ ትምህርቴን እየተማርኩ ጎን ለጎን የጥበቃ ስራ እሰራ ነበር፡፡ ጭንቅላቴ ላይ ምን የሚያህል ሄልሜት አድርጌ የጥበቃ ስራዬን በማከናውን ሰዓት አንድ ነገር ትዝ እያለኝ ይገርመኝ ነበር፡፡ አገሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ልጆች ሆነን ዘበኛ እያልን እንሳደብ ነበር፤ ይህን ብዬ ሳላበቃ በሰው ሀገር ዘበኛ ሆንኩ...››

ይህን የተናገሩት ሰው ‹ኢሲኤክስ› በሚባለው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፍተኛ የማኔጅመንት አመራርና ባለሙያ ሆነው ሀገራቸው ለሌሎች ሀገር አርአያ እስክትሆን ድረስ ሰርተዋል፡፡ ትምህርታቸውን እየተማሩ ባልመረጡትና ባላሰቡት የጥበቃ ስራ እያገለገሉ ከፍና ከፍ ወዳለ ቦታ ደርሰዋል፡፡

ዛሬ በምድረ አሜሪካ ዳያስፖራ እያልን የምንጠራው ባለሃብት ምን አይነት ድካምና እንግልት ውስጥ ገብቶ የሀገሩ ስራ ፈጣሪና ሃብታም እንደሆነ እኚህ ሰው ምስክር ናቸው፤ እኚህ ሰው በአሜሪካም፣ በአውሮፓም ካሉት ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ ከ90 በመቶ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን መወከል ይችላሉ፡፡

‹በአሜሪካ ስራ እንዴት ነው እንጂ ስራህ ምንድን ነው አይባልም› የሚሉ ብዙዎች እንዳሉ እማኝ አያሻም፡፡ ‹የተማረ ይቅበረኝ አለች ኮብል ስቶን› እንደተባለው ሁሉ ‹የተማረ ይጠበኝ አለች ሽንት ቤት ወይም ሰሃን› ለማለት የማንደፍር፣ ያልደፈርንም ሰዎች በደሃዋ አገር የተፈጠረ የስራ እድል የምንኮንነው እውነት ለወጣቱና ለትምህርት ስርዓቱ ተጨንቀን?

በሀገራችን የስራ እድል መፈጠሩ የሚበረታታ ነው እያልን ስራውን ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተማሩ ሰዎች ሊሰሩት አይገባም ብለን የምናጥላላ፣ ሀገር የፈጠረቻቸው ምሁራን ውጭ ሀገር ሄደው ዛሬ በማጥላላት ላይ ካለነው ስራ በማይተናነስ ሙያ ሲሰማሩ ምንስ ተናገርን?

በአንድ በኩል ፍልሰት የበዛው ወጣቱ ስራ አጥቶ ነው ተስፋ ቆርጦ ነው፤ ለዚህ ሃላፊነት መውሰድ ያለበት መንግስት ነው እንላለን፡፡ በሌላ በኩል ስራዎችን ሁሉ የመሃይምና ያልተማረ ሰው አድርገን እንቆጥራለን፡፡ ፊደል የቆጠረ በድንጋይ ላይ በእግሩ መሄድ እንጂ በእጁ መንካት የለበትም ስንል እንገልፃለን፡፡

ይሄ ክፉ የአመለካከት ደዌ ልበ ብሩህ በሚያደርገው የጋዜጠኝነት ተግባር ተሰማርተናል ከምንል ጀምሮ የህዝብ ጉዳይ ያገባናል የምንል በተግባር ያልገባንና ሲያገባን የማንታይ የስም

ፖለቲከኞች ጎልቶ ይታያል፡፡ የዚህ አመለካከት ችግር መሰረቱ ትምክህት ነው፡፡ ወላጆቻችን ሲያሳድጉን ስለ ስራ ባህል እያስረዱ አላሳደጉንም፡፡

በዚህም ላይ ጠባቂነት ተጠናውቶናል፡፡ እኛ መማር፣ መንግስት መቅጠር ስራው ነው ብለን ደምድመን ጨርሰናል፡፡ አለያም በተማርንበት ልክ የተሰፋ መስሪያ ቤት ካልተዘጋጀልን አንረባም፣ አንለማም ብለን ወስነናል፡፡ ስራጠል የሆንነው መስራት የማይችል ጉልበትና አዕምሮ ስላለን ግን አይደለም፡፡ በአመለካከት ችግር ህሊናችን ስለተቀፈደደ፣ አመለካከታችን እንዳይለወጥ ዕለት ዕለት የሚጎተጉቱን ስራ ጠሎች ስለሞሉብንም ጭምር ነው፡፡

የስራ ባህላችን ያኖረብንን ጠባሳ ጨምሮ ፊደል በማይፈታው የትምክህት አስተሳሰብ የበለፀግን ጥቂቶች የዩኒቨርስቲዎቻችን ልጆችና ወጣቶች በተማሩበት ሙያ የተሻለ ገቢ ሊያስገኙላቸው በሚችል ተግባር እንዲሰማሩ በሚያግዝ የካፒታል ፈጠራ ላይ መሰማራታቸው አስደንግጦናል፡፡ የደነገጥን ብኩኖች የተማርን ነን የምንል ሆነን መገኘታችን ደግሞ እኔን አስደንግጦኛል፡፡

የነገ እጣ ፈንታዬን እንዳስብና እንድጠራጠር አድርጎኛል፤ ጠርጥሬና ተጠራጥሬ ሳበቃ ግን መፍትሄው በእጄ ላይ መሆኑን ተረዳሁ፤ መፍትሄው እናንተ የስራ ነፍሰ ገዳዮችን ወጊዱ ማለት መሆኑ ገባኝ፡፡

ሲሻችሁ የትምህርት ስርዓቱ ተቆርቋሪዎች፣ ስትፈልጉ የወጣቱ ተከራካሪዎች መስላችሁ ለመታየት የምትሞክሩ ባለፊደሎች የአመለካከት ጥራት ሳይኖራችሁ ከቶ ስለ ትምህርት ጥራት መረዳትና ማወቅ እንዴት ቻላችሁ? አረ ጨፋኝ በዛ ጎበዝ?!

ለምን በደካማ አመለካከት የተበረዘን ባለ አጀንዳዎች በነገሩ ግራ ከተጋቡ ሰዎችን ማደናገርና ማስደንገጥ ላይ አተኮርን፡፡ ይልቅ ስራ ህይወት ነው ብለን በመስራት መከበር

እንደሚቻል፣ በርካታ ምሁራን ከተማሩበት ሙያ ውጪ በሌሎች ሀገሮች ብዙ ገንዘብ ሊያስገኝ ይችላል ብለን መንገርና ማነሳሳት ይገባን ነበር፡፡

ለዚህ በጎ ተግባር ያልታደለ አዕምሮ ግን ወጣቱ ምሁር በመቀጠርና በጠባቂነት ላይ ብቻ እያተኩር በርካታ የስራ አማራጮች አሉ ብሎ አቅጣጫ ያሳየን መንግስት መኮነን ስራዬ ብሎ ተያይዟል፡፡ እኔን ጨምሮ ብዙዎች በጥሩ ፅሁፉና የተሻለ ሪፖርቱ አማራጭ ነው ብለን የምናምነው ሪፖርተር ጋዜጣ በዚህ ጉዳይ ላይ ያንፀባረቀው አቋም አስደንግጦኛል፡፡ በጣም ያስደነገጠኝ ደግሞ የጋዜጣው ባለቤት አቶ አማረ አረጋዊ ስለሆኑ ነው፡፡

እሳቸው እንደሚያውቁትና እንደነበሩበት ‹‹ደርግን ለመጣል በተደረገው የ17 ዓመታት ጦርነት ዋነኛው ተሳታፊ አርሶ አደሩ ቢሆንም፣ የትግሉ ተዋናይ የተማረውም ወጣት ነበር፡፡ ከዩኒቨርስቲ 2ኛና 3ኛ ዓመት ትምህርታቸውን አቋርጠው ጫካ የገቡትን ጨምሮ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወጣቶች እኩልነትና ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ ዱር ቤቴ ብለዋል፡፡

በሙያቸው ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ ወዘተ... መሆን የሚችሉና የቻሉ ሰዎች ሳይቀሩ ፊደል ያልቆጠረ ነው ተብሎ በሀገራችን የትምክህት ሃይል ከሚተቸው አርሶ አደር ጋር እኩል ነፍጥ አንግበው፣ ምንም ትምህርት የማይጠይቀውን፣ የመተኮስ ተግባር አከናውነዋል፡፡ /መተኮስም ቢሆን ትምህርት ያሻዋል/ አምባገነኑን የድህነት ዘበኛም ጥለዋል፡፡ የድህነቱ ዘበኛ ከተወገደም በኋላ ወደሚፈልጉት ትምህርትና ሙያ ተሰማርተው መስራትም፣ ማልማትም መምራትም ችለዋል፡፡

የአሁኑ ጠላት ድህነት ነው፤ ድህነት ሀገራችንና ህዝቦቿ ወደ ኋላ አስቀርቶን ኖሯል፤ የተማሩ ዜጎቻችን ሳይቀር በውጭ ሀገር ስራ ፍለጋ እንዲንከራተቱ፣ ገንዘብ እያላቸው የሙያ መስክና አማራጭ አጥተው በየበረሃው ታሽገው ሲሞቱ ጭምር ተመልክተናል፡፡ የተማረው ብቻ ሳይሆን ያልተማረውም ጭምር ሀገር ጥሎ ሲሰደድ አይተናል፡፡

ተስፋ መቁረጡ ሁለት አይነት ነው፤ አንድም እዚሁ ሀገሬ ውስጥ ዝቅ ብዬ ከምሰራ ውጭ ሀገር ሰው በማያውቀኝ ቦታ በሀገሬ የተዋረደ ተደርጎ በሚቆጠረው ስራም ላይ ቢሆን ተሰማርቼ የተሻለ ገንዘብና ጥሪት ቋጥሬ ሀገሬ ላይ ብመለስ የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ምንም አይነት ሙያና እውቀት የለኝም፣ የተማረውም ጭምር ስራ ፈት እየሆነ ነው፤ ስለዚህ እድሌን ብኖርም ብሞትም ልሞክር ብሎ የሚጓዘው ነው፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት ብዙ ስራ መፍጠርና አማራጭ ማበራከት ግድ ይላል፡፡ መንግስት ችግሩ ውስብስብ እንደሆነ በመረዳት ሰፊውን የህብረተሰብ ክፍል፣ በተለይም ወጣቱን የሚያቅፍ በርካታ የስራ እድሎች ፈጥሯል፡፡ የስራ እድሉ ገጠር ከከተማ የሚለያይ ቢሆንም የከተማው ስራ አጥነት በከተማ ልማቱ ዋነኛ አንቀሳቃሾች በተሰባሰቡበት የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መፈታት እንደሚችል አምኗል፡፡

የተማረም፣ ያልተማረም ሊቀብራት፣ ቀብሮም በአማካይ በወር እስከ 5እና 6ሺ ብር ልታስገኝ የምትችለው የኮብል ስቶን ድንጋይ መጥረብና መቅበር ሙያ አንዱ ነው፡፡ በአረብ ሀገራት እየተሰደዱና ብዙ መከራ እየደረሰባቸው ያሉ እህቶቻችን ከሚሰሩት አድካሚና አሰልቺ ስራ ጎን ለጎን የሚደርስባቸው የፆታ ጥቃቶች ይታወቃሉ፡፡

ከዚያም ባለፈ የህይወት መስዋዕትነትም ይከፍላሉ፤ የብዙ ዓረብ ሀገሮች እውነታ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ዋጋም ተከፍሎ ከተሳካ የሚያገኙት የገንዘብ መጠን በአማካይ ከመቶ ዶላር አይበልጥም፡፡

እናም በሀገር ምድር፣ በሰላምና በጤና ሰርቶ እስከ 5ሺ ብር ማግኘት የሚቻልበት ኮብል ስቶን ለምን ተናቀ ብሎ መጠየቅ ምክንያታዊ ሆኖ የዩኒቨርስቲ ምሩቃኑ በተማሩበት ሙያ ስራ ለመፍጠር ቢሹ የካፒታል አቅማቸውን በሚያሳድገው የኮንስትራክሽን ዘርፍ መሰማራታቸው ኪሳራ ተደርጎ ለምን ታየ!?

እውነት የዚህች ሀገር ዋነኛ ጠላት ድህነት መሆኑን የተረዳን ሰዎች ይህን ጠላት የተማረው ሃይል ሙያውን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሰርቶና አሰርቶ በድንጋይ መጥረብም፣ በግብርናም በእንጨት ስራም ወዘተ… ቢያሸንፍ ማን ይጎዳል?

ደርግን ያሸነፈው አልተማረም ብለን ስንሳለቅበት የነበረው አርሶአ ደር ብቻ ነውን? ያንን ትግል የመራው ሃይል እስክሪቢቶና ወረቀት ብቻ ይዞ ነበርን? ከአርሶ አደሩ ጋር አላረሰም? የአርሶ አደሩን ሰብል አልሰበሰበም? አብሮ አልተራበም? አብሮ አልተታኮሰም? የእኔ ስራ አንተን ማታገል፣ የአንተ ስራ መመሞትና መታገል ነው ብሎ ነበርን?

ለምንድን ነው ዛሬ እየተካሄደ ባለው የፀረ ድህነት ትግል የስራ ምርጫ ውስጥ የተገባው? በስደት ከመኖርና፣ በኮንቴይነር ታሽጎ ከመሞት የባሰ ውርደት አለን? ራሱ ሪፖርተር ጋዜጣ ‹የመጀመሪያ ዲግሪና ሁለተኛ ዲግሪ ካላቸው ዜጎች በጎዳና ተዳዳሪነት ይኖራሉ› ብሎ ገልፆ ሳምንት ሳይሞላው፣ ‹የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ወጣቶች ድንጋይ ሊጠርቡ መሆኑ ተገቢ አይደለም› ብሎ የህይወትና ሞት ምርጫ ማስቀመጥ ነበረበት? ወይስ የተማረው ወጣት ሁሉ የመንግስት ቅጥር ይጠብቅ?

‹‹… *ረጅም ዕድሜውን በትምህርት ያሳለፈ አንድ ባለሙያ በተማረበት የሙያ ዘርፍ በመሰማራት ፋንታ ወደታች ወርዶ ባልተማሩ ሰዎች ሊሠራ በሚችል የሥራ ዘርፍ ሲሰማራ ማየት ለማንም የሚዋጥ ተግባር አይደለም፡፡ መንግሥት በበጀተው በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ከየዩኒቨርሲቲው ትምህርት ተከታትለው የሚመረቁ ወጣቶች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው ኮብል ስቶን ማንጠፍ ከሆነ፣ ‹‹መማር ለምን ያስፈልጋል?›› የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ሆኗል፡፡ ድሃ ቤተሰቦቹን አስቸግሮ ለዓመታት ትምህርቱን የተከታተለ ግለሰብ የመጨረሻ ሥራው ድንጋይ መጥረብ ከሆነ የመማር ጥቅሙ ምን ላይ ነው?››* ብሎ የሚተነትነው ሪፖርተር ድሃ ቤተሰቦቹንም ሀገሩንም አስቸግሮ ከተማረ በኋላ በስደት አሜሪካ በጥበቃና ሌላ የሽንት ቤት ፅዳት ላይ ሰለተሰማራው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ለምን አልቆጨውም?

የተማረው ወጣት በመንግስት ስራ ቢዘጋጅለት ኖሮስ የትምህርት ጥራቱ ተረጋግጧል ብለን እንናገር ነበርን? የትምህርት ጥራት ማረጋገጫው ስራ መምረጥ ወይስ በተማሩት የሙያ መስክ ውጤታማ አገልግሎት መስጠት? እነዚህን ጉዳዮች ሁሉም ወገን ቢያጤናቸው መግባባት ላይ ይደረሳል፡፡

የተማሩ ወጣቶች በተማሩበት ሙያ ቢሰማሩ ውጤታማ መሆን ብቻ ሳይሆን በሙያቸው የመሰማራትም መብት አላቸው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ቦታ በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገርም ተዘዋውሮ የመስራት መብት አላቸው፡፡

ስልጠናቸው ከትምህርት ስርዓቱ አኳያ /70 በ30/ ለሙያ ስራዎች ልዩ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ተደራጅተው ስራ ለመፍጠርና ለመምራት የተሻለ እድል አላቸው፡፡ የተማሩ ወጣቶች የሚሰሩትን ስራ ዘመናዊ፣ የተሻለ ገቢም የሚያስገኝ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ዛሬም የአርሶአደሩን ሙያ የምንንቅ ሰዎች ከሞዴል አርሶ አደሮች ውጤት አለመማራችን ያስተዛዝባል፡፡ በሬ ጠምዶ የሚያርስ፣ በአነስተኛ ማሳ የሚታገል ወዘተ ሲባል የነበረው አርሶ አደር ምን ያህል ጥሪት እንደቋጠረ አይተናል፡፡ የተማረውና ከገጠር የወጣው ወጣት የአባቱን ሙያ ከዘመናዊ ግብርና ጋር አስተሳስሮ ቢሰራ ጉዳት የለውም፡፡ ይህ ተግባሩ የመጨረሻ ስራው ተደርጎም ሊቆጠር አይገባም፡፡

የትላንት አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጅ ተመራማሪ ሆኖ ሀገሩንም፣ አህጉሩንም ማስጠራት ይችላል፡፡ ስራ ፈጥሮ ሀብት ማካበት፣ የተማረበትንም ሙያ ማስፋፋት ይችላል፡፡ ቁም ነገሩ የተማረው ወጣት ሙያውን እንዳይረሳ፣ መንግስትም ያወጣበትን ወጪ በሙያው አገልግሎ ለህብረተሰቡ እንዲያደርስ ምን አማራጭ *ይፈጠር የሚለውን የመለየት ጉዳይ ነው፡፡*